

# የመጨረሻው እራት

ደቀመዛሙርት ኢየሱስን “የፋሲካን እራት የት እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?” ብለው ጠየቁት። ኢየሱስም ለየት ያለ እንግዳ መልስ መለሰላቸው። ወደከተማ ሂዱና አንድ ሰው ታገኛላችሁ። ሰውዬውንም “ጌታ ጊዜዬ ደርሶአል፣ ስለዚህ የፋሲካን እራት በቤትህ ከደቀመዛሙርቴ ጋር እበላለሁ በሉት። ሰውዬውም ይገባዋል። ” ጴጥሮስና ዮሐንስም ወደከተማ ሄዱ። በከተማይቱ ጎዳና እየተራመዱ እያሉም አንድ ሰው እንስራ ተሸክሞ (ሰውዬውን የሚያውቁበት ምልክትም ይህ እንደሆነ ኢየሱስ ነግሯቸው ነበር።)

ጴጥሮስና ዮሐንስም ሰውዬው ወደሚገባበት ቤት ተከተሉት። ከዚያም ከቤቱ ባለቤት ጋር እራት ስለሚበሉበት ክፍል ተነጋገሩ። ጌታ በዚያ ስፍራ ፋሲካን መብላት እንደሚፈልግ ነገሩት። ሰውዬውም በደርብ ላይ ያለ ሰፊ ክፍል አሳያቸው። ክፍሉም በሚገባ የተዘጋጀ ስለነበር ለፋሲካ እራት የሚያስፈልገውን ነገር ማዘጋጀት ጀመሩ። ከዚህ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ኢየሱስንና ሌሎች ደቀመዛሙርትን መጠባበቅ ጀመሩ።

እራት እየበሉ እያሉም ኢየሱስ ሊፈፀሙ ስላላቸው ነገሮች ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው።
ዳቦውን ከባረከ በኋላ ቆረሰው። ለደቀ መዛሙረቱም ሰጣቸው።
እንዲህም አላቸው “እንካችሁ ብሉት፣ ይህ ስጋዬ ነው።”
ስለፅዋውም አመሰገነ። እንዲህም አላቸው “ለእናንተ የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው።”

*የመጨረሻው እራት ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 26፡ 17 – 30 እና በማርቆስ 14፡ 12 – 26 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com